23ኛ ዓመት ቁጥር 25
23rd Year No. 25

ባሕር ዳር ጥቅምት 18 ቀን 2011 ዓ.ም
Bahir Dar, October 28, 2018

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት

# ዝክረ ሕግ

# ZIKRE HIG

## Of the Council of the Amhara National Regional State in the Federal Democratic Republic of Ethiopia

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

Issued under the auspices of the Council of the Amhara National Regional State

1324
ያንዱ ዋጋ 45 ብር
Unit Price Birr 45

ማውጫ

*አዋጅ ቁጥር 262/2010 ዓ.ም*

**በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ ድርጅትን ለማቋቋም ተሻሽሎ የወጣውን አዋጅ ለመሻር የወጣ አዋጅ**

Content

**Proclamation No. 262/2018**

**A Repealment Proclamation of the Revised Water Well Drilling Enterprise in the Amhara National Regional State**

## *አዋጅ ቁጥር 262/2010 ዓ.ም*

## በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ ድርጅትን ለማቋቋም ተሻሽሎ የወጣውን አዋጅ ለመሻር የወጣ አዋጅ

በስራ ላይ ያለውን የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ ድርጅት ለማቋቋም የወጣውን አዋጅ ቁጥር 198/2004 ዓ.ም ከክልሉ መንግሥት ልማት ድርጅቶች አመሰራረት፣ አደረጃጀት፣ አመራርና ድጋፍ አሰጣጥ አዋጅ ቁጥር 236/2008 ዓ.ም ዓላማና ተልዕኮ ጋር ለማጣጣም ያመች ዘንድ በግልፅ መሻርና በደንብ መተካት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

## Proclamation No. 262/2018

## A Proclamation Issued to Repeal the Revised Water Well Drilling Enterprise in the Amhara National Regional State

WHERE AS, it has been found necessary to officially repeal the existing proclamation No. 198/2012 issued to Establish the Water Well Drilling Enterprise and replace it with Regulation in order to accommodate with the Regional State Development Enterprises Establishment, Organization, Management and Support Provision Proclamation No. 236/2016;

የአማራ ክልል ምክር ቤት በተሻሻለው የብሄራዊ ክልሉ ህገ-መንግሥት አንቀፅ 49 ንዑስ አንቀጽ(3)(1) ድንጋጌ ስር በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል፡፡

*1. አጭር ርዕስ*

ይህ አዋጅ "የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ ድርጅት ማቋቋሚያ አዋጅ መሻሪያ አዋጅ ቁጥር 262/2010 ዓ.ም ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

*2. አዋጁ የተሻረ ስለመሆኑ*

የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ ድርጅትን ለማቋቋምና ስልጣንና ተግባራቱን ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር 198/2004ዓ.ም በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡

*3. መብትና ግዴታን ስለማስተላለፍ*

በአዋጅ ቁጥር 198/2004 ለውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ ድርጅት የተሰጡት መብቶችና ግዴታዎች ይህንን የመሻሪያ አዋጅ ተከትሎ የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ መሰረት እንደ አዲስ ለሚቋቋመው ድርጅት ይተላለፋሉ፡፡

*4. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ*

ይህ አዋጅ በክልሉ መንግሥት ዝክረ-ህግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

*ባህርዳር*

*ጥቅምት 18 ቀን 2010 ዓ.ም*

*ገዱ አንዳርጋቸው*

*የአማራ ብሔራዊ ክልል ፕሬዝዳንት*

NOW, THEREFORE, the Amhara Region Council pursuant to its power vested in it under Article 49, sub-article (3) (1) of the Revised National Regional Constitution, has issued this proclamation.

## 1. Short Title

This proclamation may be cited as " A Repealment Proclamation of the Water Well Drilling Enterprise Proclamation No. 262/2018."

## 2. Repealment of the Proclamation

Proclamation No. 198/2012 issued to Establish and determine its powers and duties of the Water Well Drilling Enterprise is repealed and replaced by this proclamation.

## 3. Transferring Rights and Obligations

The rights and obligations provided in Proclamation No. 198/2012 for the Water Well Drilling Enterprise shall be transferred to the newly being established Enterprise by a Regulation which will be issued by the Regional Administration Council following this repealment proclamation.

## 4. Effective date of the Proclamation

This proclamation shall come into force since its publication date in the Zikre-Hig Gazzete of the Regional State.

**Done at Bahir Dar**

**This ……. Day of October 2018**

**Gedu Andargachew**

**President of the Amhara National Region.**